# የጠበቆች የሥነ-ምግባርደንብ አፈፃፀም ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች

## ኪንግስ ሆቴል

ግንቦት 26 ቀን 2009 ዓ.ም.

- **የስብሳበው አጀንዳ/ርዕሰ-ጉዳይ፡ የጠበቆች የሥነምግባር ደንብ አፈፃፀም ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫዎች**
- **ጽሑፍ አቅራቢዎች፡-** 1. አቶ ፈቃዱ ደምሴ - በፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
  2. አቶ አበበ አሳመረ - የሕግ አማካሪና ጠበቃ
- **አወያይ፡-** አቶ በሻዳ ገመቹ - የኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር ፕሬዝዳንት
- **የስብሰባው ቦታ፡-**ኪንግስ ሆቴል
- **በአውደጥናቱ ላይ የተገኙ፡-** ጠበቆች፣ የማኅበሩ አባላትና ሌሎችም
- **የአውደጥናቱ ቀን፡-** ግንቦት 26 ቀን 2009 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 እስከ ከቀኑ 7፡30 ሰዓት

**አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት**



የማኅበሩ ፕሬዝዳንት የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከተለያዩ ባለድርሻ የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የተለያዩ የእርስ በእርስ መማማሪያ መድረክ በመፍጠር እና ሥነ-ሕግን በማሳደግ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ላይ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የእለቱ የውይይት ርዕስ የጠበቆች ሥነምግባርን የሚመለከት ሲሆን በጉዳዩ ሁለት ጽሑፎች የሚቀርቡ መሆኑን የመጀመሪያውን የፌደራል ጠ/ዐ/ሕግ የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ፈቃዱ ደምሴ በቀጣይም የማኅበራችን የቀድሞ ፕሬዝዳንት እንዲሁም የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑት አቶ አበበ አሳመረ ሲሆኑ በአወያይነት መድረኩን የሚመሩልን ደግሞ አቶ በሻዳ ገመቹ ናቸው ብለዋል፡፡ ማኅበራችን ተከታታይ የትምህርት

መርሃግብሮችን ሲያዘጋጅ በተለያዩ ፈቃደኛ ግለሰቦችና ድርጅቶች ስፖንሰር የሚደረግ ሲሆን የዕለቱን መድረክ ወጭ በመሸፈን ትብብር ያደረገልን ቤት ወገን ሊሚትድ እና አቶ በዛወርቅ ሺመላሽን እንዲሁም የማኅበሩን ጥሪ አክብረው በውይይቱ ላይ የተገኙ ባለሙያዎችን በማመስገን እና የዕለቱ ውይይት የተሳካ እንዲሆን በመመኘት የስብሰባውን በይፋ መከፈት አብስረዋል።

## አቶ በሻዳ ገመቹ - አወያይ

ጽሁፍ የሚቀርበው በሁለት ባለሙያዎች መሆኑን ጠቁመው ሁለቱም ጽሑፎች በጠበቆች ሥነ-ምግባር ላይ የሚያተኩሩ መሆኑን በመግለጽ ለሁለቱም ባለሙያዎች እያንዳንዳቸው በግማሽ ሰዓት ገለፃቸውን አቅርበው እንዲያጠናቅቁ ማሳሰቢያ ከሰጡ በኋላ ሰፊው ጊዜ ለውይይት መቅረት እንዳለበት አጥብቀው በመግለፅ በቀጥታ ወደ ጽሑፍ አቅራቢዎች መድረኩን አሳልፈው ሰጥተዋል።

## አቶ ፈቃዱ ደምሴ - ጽሑፍ አቅራቢ (በፌ/ጠ/ዐ/ሕግ የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር)



የተሰጣቸው ጊዜ አጭር በመሆኑ አንድ አንድ የመግቢያ ነጥቦችን የሚያልፏቸው መሆኑን ጠቁመው የጽሑፋቸው ውጤት በዋናነት የጥብቅና ሥነ-ምግባር፣ በጥብቅና ፈቃድና አስተዳደር እና በጠበቆች የሙያ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የተለዩ ምቹ፣ አስቻይ፣ ሁኔታዎች፣ ችግሮች፣ መንስኤዎችና መፍትሔዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል።

## *1. የሥነ-ምግባር ምንነት*

*ሥነ-ምግባር ወይም ኤቲክስ* /Ethics/ *የሚለው ቃል የተገኘው ኤቶስ* /Ethos/ *ከሚባለው የግሪክ ቃል የመጣው ኤቶስ በሚለው ሰዎች በጋራ በኅብረት የሚኖሩበትን ሥፍራ ላይ ልማድን፣ አነጋገርን፣ የአስተሳሰብ ዘይቤን፣ ጠባይን ወይም ባህሪን በመወከል የሚያገለግል ማስተማሪያ እንደሆነህመር የተባለው ፀሐፊ ያስቀመጠ መሆኑን ኤቲክስ ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የአማርኛው ትርጉሙ ሥነ-ምግባር የሚለውን ሲሆን ትርጉሙ እና ጽንሰ-ሀሣቡ ምን እንደሆነ ምሁራን በተለያየ ጊዜ በይዘት የሚመሳሰሉ፣ ነገር ግን በአገላለጽ የተለያዩ ትርጉሞች የሰጡ መሆኑን ጠቁመው ከነዚህም መካከል ካርተር የተባለው ምሁር ትክክል ወይም ስህተት ማለት ምን እንደሆነ ለማወቅ የምንጠቀምበትና ትክክል የሆነውን ማድረግ ማለት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን በጥቅሉ ሥነ-ምግባር የሰውን ተግባር፣ ባህሪይና ጠባይ ከግብረ-ገብ አንፃር ትክክልና ስህተት በማለት የሚገልጽ እንደሆነና ባህርያት ወይም ድርጊቶች መቼ ተቀባይነት እንደሚያገኙና እንደሚያጡ የሚያመለክት መለኪያ* /Standard/ *ወይም የሕጐች ስብስብ እንደሆነ፣ የሰው ልጅን፣ የአንድን ግለሰብ ወይም የሙያ አባላትን ባህሪያት የሚገዙ መርሆዎች እንደሆነ የሚገልጹ ናቸው ያሉት አቶ ፈቃዱ ነውርና ክብር፣ ክፋትና ደግነት፣ ጥሩነትና መጥፎነት፣ እንዲሁም ስለ ሥነ-ምግባር ጽንሰ ሃሳቦች ትክክለኝነትና ስህተትነት፣ ምንነት፣ መስፈርትና አስፈላጊነት የመሳሰሉትን ሃሳቦች የሚያጠና ዓቢይ የፍልስፍና ዘርፍ ሥነ-ምግባር* (Ethics) *የሚባል ስለመሆኑ አስገንዝበዋል፡፡*

## 2. *የሥነ ምግባር ምንጮች* /Sources of Ethics/

*የሥነ-ምግባር አመጣጥ ከተለያዩ ኃይማኖቶች/እምነቶች/፣ ከባህል፣ /ልማድ/ ከቤተሰብና ከዕድሜ እኩዮች አካባቢም ጋር የተያያዘ መሆኑን በዚህ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች የሚጠቁሙ ስለመሆኑ አውስቷል፡፡ ሥነ-ምግባር ከኃይማኖት እምነቶች፣ የግል ከሆነ ህሊና ውስጥ ያለፉና በጐ ነገርን የመለየት ችሎታ ይመነጫል፡፡ መልካም ነገር ማለትም እንዳንሰርቅ፣ በሐሰት እንዳንመሰክር፣ እንዳናመነዝር፣ ወዘተ እንድንፈፅም ይመክራሉ ያልተገቡ ሥነ-ምግባራዊ ድርጊቶችን እንዳንፈፅም ያስተምረናል ብለዋል፡፡ ባህልም ከማህበራዊ /ግብረገባዊ ማንነት/ ተመሳሳይነትና ከልማድ የሚነጭ እና ባህላዊ እሴቶችን የሚያካትት ሲሆን በባህል ላይ ተመስርተው የሚዳብሩ ጠቃሚ እሴቶችንም ይጨምራል፡፡ ለምሣሌ:- ታማኝነት፣ ሀቀኝነት፣ ግልጽነት ወዘተ በማለት ያብራሩ ሲሆን ከቤተሰብ በግል የተቀረጹ ተሞክሮዎችና የወላጆች መልካም እሴቶች በልጆች ዘንድ ለመልካም ሥነ-ምግባር መፈጠር መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የዕድሜ እኩዮች ወይም ጓደኞች በአካባቢያቸው ላይ በሥነ-ምግባር*

በጎም መጥፎም ተፅዕኖ መፈጠር ይችላሉ፡፡ አካባቢም ከሚፈጥረው በጎ ወይም በጎ ያልሆነ ተጽእኖ የህብረተሰቡ ወይም የግል እሴቶችና ደረጃዎች መልካም ወይም መልካም ያልሆነ ሥነ-ምግባር ሊመነጭ እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

ሌላው የሥነምግባር ምንጭሕግ ሲሆን የሰው ልጆች ባህሪ በመልካም ሁኔታ እንዲቀረፅ በማድረግ የሥነ-ምግባር ምንጭ ሆኖ ያገለግላል ያሉት ጸሑፍ አቅራቢው ሕግ በጐና በጐ ያልሆነ፣ ተቀባይነት ያለውና የሌለውን ሥነ-ምግባር በመለየት በጐ ምግባር ተፈፃሚ እንዲሆን መልካም ያልሆኑና ለሞራል ተቃራኒ የሆኑ ሥነ-ምግባሮች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ በተለያዩ ዋናና ሥነሥርዓት ህጐች ተደንግጐ ይገኛል ብለዋል፡፡ ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ድርጊቶች ለሞራል ተቃራኒ ከመሆናቸውም በላይ የሚያስቀጡ ስለመሆናቸው በተለያዩ ሕጐች የተደነገገውን ተላልፎ የተገኙትን በአግባቡ ተጠያቂ በማድረግ የሕዝብና የሀገሪቱን ሠላምና ደህንነት እንዲጠበቅና መልካም ዜጋ እንዲፈጠር በማድረግ የሥነ-ምግባር ምንጭ ሆኖ ያገለግላል ብለዋል፡፡

### 3. የሥነ-ምግባር መርሆዎች

በሀገራችን የተለመዱት የሥነ-ምግባር መርሆዎች ወደ አሥራ ሁለት የሚሆኑና እያንዳንዳቸውም የየራሣቸው ይዘትና መገለጫ ቢኖራቸውም እጅጉን የተቆራኙና አንዱ ከሌላው የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ባህሪይ እንዳላቸው አስታውሰው እነዚህን ባህሪያት/መገለጫ/ ለመገንዘብ ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን ግልፅ ለማድረግና ከጥብቅና ሙያው ጋር በተያያዘ በዝርዝር ያስቀመጡ ሲሆን እንሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1) *የተሟላ ስብዕና(Integrity)፡-* ሁለንተናዊ ውስጣዊ ሙሉነትን ማለትም እውነተኛነትን፣ ቀጥተኛነትን፣ ጥንካሬንና ጽናትን የሚያመላክት ጽንሰ ሃሳብ እንደሆነ ገልፀው እሴቶቹም ለተገልጋዮች ወይም ለዜጐች ተገቢውን ክብር መስጠት፣ ትክክለኛ ምክርና አስተያየት መስጠት፣ እንዲሁም የሀገርን ጥቅም ከሚጐዳ አሠራር መራቅ ያካትታል፡፡
2) *ታማኝነት(Loyality)፡-* የገቡበትን ቃል መጠበቅና ማክበር፣ ህጉን በአግባቡ ወይም ያለአድልዎ ሥራ ላይ ማዋል፣ የስራ ባልደረቦቻቸው የሚፈጽሟቸውን ሕገወጥ ድርጊቶች እና የሥነ-ምግባር ጥሰቶች ማሣወቅ፣ ከኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት በመራቅ አመኔታ ያለው ተግባር መፈፀምን እንደሚያካትት ጠቁመዋል፡፡
3) *ግልፅነት(Transparency)፡-* ሕብረተሰቡ ሊያውቀው የሚገባንና በምስጢር ሊያዝ የማይገባውን መረጃ መደበቅ እንደማይገባ፤ አንድ መረጃ በምስጢር ሊጠበቅ የሚገባው አግባብ ባለው ሕግ

መሠረት ምስጢር የተባለ ሲሆን እንደሆነ ገልፀው ለሚሰጧቸው ውሣኔዎች እና አገልግሎቶች ግልጽ እና ምክንያታዊ መሆን፣ ውሣኔያቸውን ወይም የሚሰጡትን አገልግሎት አስመልክቶ ከተጠቃሚው ጥያቄ ሲቀርብላቸው መረጃው በምስጢር የሚጠበቅ ካልሆነ በቀር ሕግና መመሪያን ተከትለው ተገቢውን ማብራሪያ ወይም ምላሽ መስጠት ተገቢ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

4) ***ምስጢር መጠበቅ(Secrecy)*** ፡- ምስጢራዊ የሆነን የባለጉዳይን መረጃ አለማውጣት፣ በሥራ አማካኝነት የታወቀንና ምስጢር ተብሎ የተደነገገን ጉዳይ አለመግለፅና ለግል ፍጆታና ጥቅም አለማዋልን የሚያካትት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

5) ***ሀቀኝነት(Honesty)፡-*** ለጓደኛ፣ ለሥራ/ለሙያ፣ ለመንግሥት፣ ለሀገር፣ ለገቡት ቃል ኪዳን ወዘተ ሳያወላውሉ ጸንቶ መቆምን፤ ከአታላይነትና ከአጭበርባሪነት ነፃ በመሆን ግዴታን በአግባቡ በመወጣት፤ ሥራን በሙያ ብቃትና ክህሎት በሙሉ ጉልበትና ጥንቃቄ በማከናወን፤ የሙያ ነፃነትን ጠብቆ ፍትሀዊ አገልግሎት መስጠት፣ ተገልጋዮችን በማጉላላት ለአላስፈላጊ ድርድር በሚያመች ሁኔታ የሙያ ተግባርን አለመፈፀም፤ መልካም ሥነምግባር በማሳየት ሥራን በሙያዊ ብቃት፣ ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን የሚያካትት ስለመሆኑ ዘርዝረዋል፡፡

6) ***ከአድልዎ ነፃ መሆን /አለማዳላት/(Impartiality):-*** ዜጐችን/ተገልጋዮችን/ በእኩል ማየትና በመካከላቸው ልዩነትን አለመፍጠር፣ ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን በመከተል በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር/ብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካባቢነት፣ በጋብቻ በዝምድና ወይም በሌላ አቋምና አግባብነት በሌለው ግምት ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሳያደርጉ ስራቸውን በማከናወን ፍትሓዊ አገልግሎት መስጠትን የሚያቅፍ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

7) ***ህግን ማክበር(respecting the law):-*** የሕግ የበላይነት በማይከበርበት ሁኔታ ጉልበተኛና ገንዘብ ያለው ብቻ የሚፈነጭበት፣ በዜጐች መካከል ልዩነት የሚፈጠርበትና ሥርዓት አልበኝነት የሚነግስበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ሕግን አክብሮ መስራት፤ የሕግ መንግሥቱ ድንጋጌዎች፣ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ማክበርና ማስከበር፤ የሕግ የበላይነትን በማክበርና በማስከበር ሕብረተሰቡና መንግሥት አመኔታ እንዲኖራቸው ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይገኙበታል ብለዋል፡፡

8) ***መልካም አርአያ መሆን(Examplary):-*** ከያዙት ኃላፊነትና ለህብረተሰቡ ከሚሰጡት አገልግሎት አኳያ በሥራ ቦታቸውም ሆነ ማኅበራዊ ሕይወታቸው የሚያሳዩት ሥነ-ምግባር በሥራ ባልደረቦችና በሕብረተሰቡ የሚጠበቅባቸውን ከፍ ያለ የአርአያነት ጠባይ ማሣየት፤ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማቸው፣ የተሻለለ ውጥን የሚደግፉ፣ የስራውን መልካም ስም የሚጠብቁና መተማመን ስር እንዲሰድና ፀንቶ እንዲቆይ ማድረግ፤ ህብረተሰቡ በሚያደርገው ሁለገብ

እንቅስቃሴ ውስጥ ተሣትፎ በማድረግ ውጤታማ ተግባር በመፈፀም መልካም አርአያ መሆን እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል፡፡

9) *ተጠያቂነት(Accountablity):-* ለሚያከናውኗቸው ሥራዎች ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ፤ ሥራቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ምላሽ እንዲሰጡ ተገቢ ጥያቄ ሲቀርብላቸው አስፈላጊውን ማብራሪያ የመስጠት ግዴታ፤ ለሚያከናውኗቸው ሕገ-ወጥ ስራዎች ተጠያቂ መሆን፣ በተፈለጉ ጊዜ መገኘት ወይም መቅረብን ያካትታል ብለዋል፡፡

10) *በህዝብ አገልጋይነት መንፈስ መሥራት (Serving the public):-* ባለጉዳዮችን በጥሞና በማዳመጥ፣ በማክበር እና በትህትና ላቀርቡላቸው ጉዳዮች ወይም ለሌሎች ጥያቄዎቻቸው በወቅቱ መልስ መስጠት፤ የሚያከናውናቸው ሥራዎች ሕግንና አሠራርን መሠረት አድርጎ የማከናወን፤ ለህዝብ የተገባውን ቃል በማክበር ለእንግልት፣ ለወጪ/ለኪሳራ/ ያለመዳረግን ይጨምራል ብለዋል፡፡

## 4. የፌዴራልፍ/ቤቶች ጠበቆች የሙያ ሥነ-ምግባር

### *4.1. የሙያ ሥነ-ምግባር ምንነት*

ሕብረተሰቡ በተለያየ ደረጃ የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት በየዘርፉ የተለየ እውቀትና ችሎታ ያላቸውን ሙያተኞች የሚሻ ስለመሆኑ የገለፁት ጽሑፍ አቅራቢ ይህ እውቀት በአግባቡ ከተጠቀሙበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ደግሞ ሊጎዳ ይችላል ብለዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ሙያተኞች ያላቸውን እውቀት፣ ክህሎትና ችሎታ ለሕብረተሰቡ ጠቀሜታ እንዲያውሉትና ህብረተሰቡ የጣለባቸውን አመኔታ እንዲጠብቁ በአንድ የሙያ መስክ የተሰማሩ ሙያተኞች የሚመሩበት የሚከተሉትና የሚተዳደሩበት የሥነምግባር ደረጃ ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም የሙያ ሥነ-ምግባር በአንድ የሙያ ዘርፍ የተሰማሩ አባላት በጋራ የሚመሩበት የሚከተሉትና የሚተዳደሩበት ራሳቸውንና ስራቸውን ለመቆጣጠር የሚያግዝ የሥነ-ምግባር ደረጃን የሚያመለክት መርህ ወይም ደንብ በማለት የገለፁ ሲሆን በሌላ አነጋገር በአንድ ሙያ የተሰማሩ ሙያተኞች እውቀታቸውንና ችሎታቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ሙያዊ ግዴታቸውንና ሀላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ አቅጣጫ የሚያሲዝና የሚገዙበት ደንብ ማለት ነው ሲሉ ሰፋ በማድረግ አስቀምጠዋል፡፡

### *4.2. የሙያ ሥነ-ምግባር ጠቀሜታዎች*

የሙያዊ ሥነ-ምግባር የተለያየ ጠቀሜታዎች ያሉት መሆኑን ገልፀውተቀባይነት ያላቸውን ደንቦች በጋራ በማዘጋጀት ለመጠቀምና ሙያዊ ወጣ-ገባነትን ለማስቀረት፤ ከሙያው የሚጠበቁ ኃላፊነቶችንና

ግጼታዎችን ለማመላከት፤ ቁጥጥር ለማድረግና የደንበኞችንም ሆነ የባለሙያዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፤ የላቀ ሙያዊ ሥነምግባር ያላቸውን እውቅና ለመስጠትና ሌሎቹን ለማበረታታት፤ በሙያው የሚነሱ አስቸጋሪ ጉዳዮችን በጋራ መፍትሔ ለማፈላለግ፤ ሙያዊ ጥራትን ለማስጠበቅ እና ለማስቀጠል ወዘተ በማለት ጥቅሞችን ዘርዝሯል።

### *4.3. የጥብቅና ፈቃድና አስተዳደር ስራዎችን ለመምራት ያሉ አስቻይ ሁኔታዎች*

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 6/11 ጠ/ዐቃቤ ሕግ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ደረጃ የጥብቅና አገልግሎት ለሚሠጡ ጠበቆች በሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ያድሳል፤ ጠበቆችና የጥብቅና አገልግሎትን ያስተዳድራል ... የሚል ድንጋጌ ያለ መሆኑን ጠቅሰው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 መውጣቱ እንዲሁም ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/1992 መኖሩ፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92ን ለማስፈፀም መመሪያ ቁጥር 1/1992 መውጣቱ፤ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ጉዳዮችን የሚመለከቱ የተለያዩ አደረጃጀቶች መኖራቸውና ስራውን በመስራት ላይ የሚገኙ መሆኑ፤ የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ፣ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና አዘጋጅና የችሎታ መለኪያ ቦርድ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ መዋቀሩ፤ የጥብቅና ፈቃድና አስተዳደርን ስራን የሚመራ ራሱን የቻለ የጥብቅና ፈቃድና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እንዲኖር መደረጉ፤ የፍትህ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የገንዘብ አቅም ለሌላቸው ዜጎች ጠበቃ በመመደብ በፍትህ አደባባይ በእኩልነት ተስተናግደው መብቶቻቸው እንዲከበር እየተደረገ መሆኑ፤ በተለይ ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋውያን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እየተቻለ መሆኑ፤ አብዛኞቹ ጠበቆች ሙያውንና የስነምግባሩን ደንቡን ጠብቀው እየሰሩ የሚገኙ መሆኑ፤ ከጠበቆች ማህበራት ጋር በጋራ ለመስራት እንቅስቃሴ መኖሩ፤ የግልፀኝነትና ተጠያቂነት አሰራር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ፣ ወዘተ አስቻይና ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን በዝርዝር አስቀምጧል።

### *4.4. በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ /በዳይሬክቶሬቱ/ በኩል የሚታዩ ውስንነቶች ወይም ችግሮች*

ሁሉንም ጠበቆች በአቅም፣ በአመለካከትና በሥነ-ምግባር ለመገንባት ሥልጠና በመስጠት ረገድ ውስንነት ያለ መሆኑ፤ በጠበቆች ላይ የሚቀርብ የዲሲፕሊን ክስ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዲሲፕሊን ጉባኤ የውሳኔ ሀሳብ መዘግትና አልፎ አልፎ የውሳኔ ሀሳብ ጥራት መጓደል መኖር፣፤ የነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ሁሉም ጠበቆች አገልግሎቱን እንዲሰጡ በማድረግ ወጥነት

የሌለ መሆኑ በተለይ የ50 ሰዓት የግዴታ የነፃ አገልግሎት በአዲስ አበባ እና ክልል፤ ጠበቆችን በችሎትም ሆነ በስራ ቦታ በመገኘት የሙያውን ሥነ-ምግባር ጠብቀው ስለመስራታቸው ክትትልና ድጋፍ ያለማድረግና ስራው በቢሮው ውስጥ መወሰኑ፤ በተለያዩ ጉዳዮች በተለይም በሥልጠና፣ በሕግ ማርቀቅ፣ በጥናት፣ በምርምር ወዘተ ላይ አቅምና ተነሳሽነት ያላቸውን ጠበቆችና ማኀበራት ያለመጠቀም ችግሮች ተለይተዋል ብለዋል፡፡

### 4.5. በጠበቆች በኩል የሚፈፀሙ ዋና ዋና ችግሮች

በጠበቆች በኩል የሚታዩ መሠረታዊ ችግሮችን አስመልክቶ ጽሑፍ አቅራቢው ያነሷቸው ነጥቦች መካከል የጥብቅና ፈቃድን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ወቅቱ ያለማሳደስ፤ ብቃት ያለው ሙያዊ አገልግሎት ለደንበኛ ያለመስጠት (በማማከር፣ በክስ ዝግጅት፣ በመልስ፣ በመልስ መልስ፣ በችሎት ክርክር፣ በይግባኝ ወዘተ)፤ ከደንበኛ ጋር ውል ሳይዋዋሉ አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ውል ተዋውሎና ገንዘብ ተቀብሎ መጥፋት፤ ለደንበኛ ተገቢ መረጃ ያለመስጠት፤ በራስ ተነሳሽነት ነጻ የሕግ አገልግሎት ለመስጠት የሚደረገው እንቅስቃሴ ውስን መሆንና ለተሰጠ አገልግሎትም ሪፖርት በማቅረብ ረገድ ክፍተት መኖር፤ ለደንበኛው፣ ለችሎት፣ ለተከራካሪው ወገን ተገቢውን ክብር ያለመስጠት፤ የጉዳዩን ፍሬ ነገርነ ማስረጃዎችን መሠረት አድርጎ ከመስራት ይልቅ አላስፈላጊ የሆነ ክርክር እናማስረጃዎችን በማቅረብ የፍርድ ሂደቱ እንዲጓተት እንዲሁም ተገልጋይ እንዲጉላላ ማድረግ፤ ከአገልግሎት ጠያቂው በሚቀርብ አዲስና ውስብስብ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀትና ክህሎት ሳይኖር ተቀብሎ ጉዳዩ ውጤት እንዳይኖረው ማድረግ፤ ጠበቆችም ሆኑ የጠበቆችም ማህበራት በጠበቃ የሚፈፀም የሥነምግባር ጥሰትን ለሚመለከተው አካል ያለማሳወቅ፤ በጠበቆች ላይ የሚነሱ ችግሮችን አይቶና ተቀብሎ ለማስተካከል ጥረት ከማድረግ ይልቅ ችግሮቹን የውጫዊ አካል ችግር ብቻ አድርጎ የማቅረብ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡

### 4.6. ደንበኞችና ህብረተሰቡ በጠበቃ ላይ ያላቸው አመለካከት

ተገልጋዩ በጠበቃው ላይ የሚያነሰው ወይም ሕብረተሰቡ በጠበቃው ላይ የሚፈፅመው ተግባርን በሚመለከት ዝረዝር ነገር ያቀረቡት አቶ ፍቃዱ ሁሉም ጠበቆች የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚሰሩ ሳይሆን የገንዘብ ጥቅማቸውን ብቻ ለማስጠበቅ ብቻ የሚሯሯጡ አድርጎ ማየት፤ ጠበቃው ሙያውን ብቻ መሰረት አድርጎ ከመስራት ይልቅ ከውሳኔ ሰጭ አካላት ጋር በመቀራረብ ጉዳዩን ለእርሱ በሚመች ሁኔታ ለማስወሰን ጥረት ያደርጋል፤ ለጠበቃው ተገቢ የሆነ ክብር ያለመስጠት፤ ደንበኛ ጉዳዩ ካለቀለት በኋላ ለጠበቃው በውሉ መሰረት ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ያለመስጠት፣ ጠበቃው በችሎት

ላለመናገር ምክንያት ኖሮት ዝም ቢል ደንበኛው ጠበቃዬ ዝም ያለው ለተቃራኒዬ ወግኖ ነው በሚል ቅሬታ መያዝ፤ ጥሩ ክፍያ ካገኙ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ይሰራሉ፣ ካላገኙ ብዙም ግድ የላቸውም፣ ብዙ ጉዳዮችን ይዘው ሲደራረብባቸው ቀጠሮ እንዲተላለፍ ያደርጋሉ፣ በቀጠሮውም ላይገኙ ይችላሉ፣ ደንበኞች በራሳቸው ፍላጎት ላይ ብቻ በመመስረት ጠበቆች ከሕግና አሠራር ውጪ ጉዳያቸው ውጤት እንዲያመጣ ማድረግ የጠበቆች ግዴታ አድርጎ መውሰድ/በትውውቅ፣ በገንዘብ፣ በኔትዎርክ ወዘተ እንዲሰራ/፤ ጉዳይን(መዝገብን) ወደሚፈልገው ዳኛ እንዲቀርብ ያደርጋል፤ የፍርድ ቤት ቀጠሮዎች እንዲፋጠኑ ወይንም እንዲዘገዩ፣ እንደዚሁም መዝገቦች ያለ ቦታቸው እንዲቀመጡ ያስደርጋሉ፤ ምስክሮች ወይም ኤክስፐርቶች በአንድ ጉዳይ ላይ የምስክርነት ቃል ወይም ማብራሪያ እንዳይሰጡ በጥቅም በመደለል የተዛባ ወይም ከእውነታ የሚቃረን ምስክርነት ወይም ማብራሪያ እንዲሰጥ ያስደርጋሉ በማለት በዝረዝር አስረድተዋል፡፡

### *4.7. በጠበቆችና በማኅበሩ በኩል የሚነሱ ችግሮች*

አንድ አንድ ጠበቆች ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ጠበቆች እንዲቀጡ ትኩረት አድርጎ ይሰራል የሚሉ አሉ፤ ፍርድ ቤቶች ጠበቆችን ከዐቃቤ ህግ፣ ከፖሊስ፣ ከነገረ ፈጅ ጋር በእኩል አይን በማየት አገልግሎት አይሰጠንም፤ ያለንን አጀንዳ አይተን የፍርድ ቤቱን ችሎት ቀጠሮ ስንጠይቅ አጀንዳ የምንይዘው ጠበቃውን አማክረን አይደለም በማለት ያመናጭቁናል፤ ፍርድ ቤት ያለበቂ ምክንያት ተደጋጋሚ ቀጠሮ እየሠጠ ለደንበኞችን ፈጣን ፍትህ ማግኘት ላይ ችግር እየተፈጠረ ይገኛል፤ በፍርድ ቤት መዝግብ ለማስከፈትም ሆነ የውሳኔ ግልባጭ ለማግኘት ውጣ ውረድ አለብን፣ ለደንበኞች ተመሳሳይ ጉዳይ ይዘን በፍርድ ቤቶች ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ውሳኔ እየተሰጠ አይደለም፤ ደንበኛን በፖሊስ ጣቢያም ሆነ በማረሚያ ቤት ለማነጋገር ስንፈልግ በአስተዳደሮቹ ተገቢ ድጋፍ አያደርግልንም፣ በቀጠሮ ያመላልሰናል፣ አመቺ ቦታና በቂ ጊዜ አይሰጠንም፤ የሚፈለግብንን ግብር በወቅቱ ለመክፈል ገቢዎችና ጉምሩክ ስንሄድ ቶሎ ባለማስተናገድ በቀጠሮ ያመላልሱናል፤ የነፃ የህግ እንድንሰጥ ጉዳይ ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተሰጥቶን ፍርድ ቤት ስንቀርብ ከተገልጋይ ጋር ተዋውላችሁ የውክልና ውል ከሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አምጡ ስለሚባል ባለጉዳይ ለውክልናው ገንዘብ ከፍሎ ማምጣት ችግር አለ፤ የነፃ የህግ እንድንሰጥ በሚደረግ ጉዳይ ለሚያስፈልግ አንዳንድ ወጪዎች ባለጉዳይ እኛ እንድንከፍልና ማስረጃዎችን ራሳችን ከያለበት ፈልገን እንድናቀርብ የመጠበቅና ወጪውን እንዲሸፍን ሲጠየቅ አግባብ ያልሆነ ስም ይሰጠናል በማለት ያሉትን ችግሮች በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡

## 5. ጠበቆች መከተል ያለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

ጠበቆች ሕግን በማክበር፣ በማስከበርና ፍትህን ለማስገኘት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሙያ ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን ሲወጡ መከተል ካለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከልጥብቅና ፈቃድን በወቅቱ ማሳደስ፤ ከደንበኛ ጋር በጽሑፍ የሰፈረ ግልፅ የውል ስምምነት መፈፀም፣ (የአገልግሎት አይነትና የክፍያ መጠን)፤ ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት፤ ለደንበኛው ጉዳዩ የደረሰበትን ሁኔታ የማሳወቅና መረጃ መስጠት፤ የደንበኛውን ሚስጢር መጠበቅ፤ ለደንበኛ ገንዘብ ያለማበደር ወይም ከደንበኛ ገንዘብ አለመበደር፤ የጥቅም ግጭት ባለው ጉዳይ ውስጥ ገብቶ የሙያ አገልግሎት ያለመስጠት፤ ቀደም ሲል በዳኝነት ወይም በሽምግልና ዳኝነት ወይም በአስታራቂነት በተሳተፉበት ጉዳይ በማናቸውም ሁኔታ የጥብቅና አገልግሎት ያለመስጠት፣ ቀደም ሲል በመንግስት ስራ እያለ በቀጥታ በወሰነባቸው ወይም በጥልቀት በተሳተፈባቸው ጉዳዮች ላይ ከቀድምሞ አሰሪው ጋር ተመካክሮ የፅሁፍ ፈቃድ ከልተሰጠው በስተቀር ለደንበኛው የሙያ አገልግሎት አለመስጠት፤ ከደንበኛ የቀረበን ጉዳይ አይቶ ለቀጣይ ስራ ሕጋዊ መሰረት የሌለው ከሆነ ጉዳዩን አለመያዝ፤ ሌላውን ወገን ለመጉዳት በማሰብ በክፋት ክስ ወይም ክርክር አለማቅረብ፤ በግልፅ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ አግባብነት ያለው አስመስሎ ለፍርድ ቤት አለማቅረብ፤ ነፃ የሕግ አገልግሎት መስጠትና የመሳሰሉት ናቸው በማለት አስቀምጠዋል፡፡



6. የመፍትሔ ሀሳቦች

ከላይ ለተነሡ ተጨባጭ ችግሮች የመፍትሔ ሃሳቦች ያስቀመጡ ሲሆን እነዚህም እንሚከተለው ተሰድረዋል፡፡

- ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ከጠበቆችና ከጠበቆች ማኅበራት ጋር ለሕግ የበላይነት መከበር ተደጋግፎና ተቀናጅቶ መስራት፤
- ለጠበቆች በህገ መንግስቱ መርሆዎች፣ በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ያሉ ችግሮችና አደጋዎች እና በሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና በመስጠት የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ሁለንተናዊ ግንዛቤ ይዘው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በጠበቆች የስራ ቦታና በችሎት በመገኘት  የድጋፍና ክትትል ስራ መስራት፤
- የጠበቆች ማህበራት በፍትህ አካላት የጋራ መድረክ ላይ እና በህዝብ ክንፍ አደረጃጀት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የነቃ ተስትፎ እንዲያድርጉ ማድረግ፤
- ጠበቆች የባለጉዳዮች ወኪል ብቻ ሳይሆኑ የፍትህ አስተዳደሩም አካል በመሆናቸው ፍ/ቤቶች እውነት ላይ ደርሰው ፍትሃዊና ሚዛናዊነትን የተላበሰ ውሳኔ እንዲሰጡ  የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው፤
- የጠበቆች ማህበራት ለአባሎቻቸው አስፈላጊ ጉዳዮችን በመለየት በአመለካከት፣ በእውቀት፣ በክህሎትና በሥነምግባር ጥሩ አቅም እንዲኖራቸው ስልጠና መስጠትና የተሞክሮ ልምድ ለውውጥ ማድረግ፤
- በሚደረጉ ዘርፈ ብዙ እቅስቃሴዎች ጠበቆችንና የጠበቆች ማኅበራት አቅም መጠቀምና ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ (በስልጠና፣ በሕግ ማርቀቅ፣ በጥናትና ምርምር)፤
- በስራ ላይ ያሉ የጥብቅና ፈቃድ አሰጣጥ አዋጅንና የስነምግባር ደንቡን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ታይቶ እንዲሻሻሉ ማድረግ፤

በመጨረሻም ጠበቆች ህግን ለማስከበርና ፍትህን ለማስገኘት የፍትህ አስተዳደሩን የማገዝ ኃላፊት እንዳለባቸው የሚታወቅ ሲሆን ይህንንም ተግባራቸውን ሲወጡ ሙያዊ ነፃነታቸውን በመጠበቅ፣ ለደንበኛቸው ብቃት ያለው አገልግሎት በመስጠትና ለፍትህ አስተዳደሩ ያለቸውን ታማኝነት በማይሸረሽር መልኩ መሆን አለበት ያሉት አቶ ፍቃዱ ጠበቆች የባለጉዳዮች ወኪል ብቻ ሳይሆኑ

የፍትህ አተዳደሩም አካል በመሆናቸው ፍርድ ቤቶች በእውነት ላይ እንዲያደርሱና ፍትሃዊና ሚዛናዊነትን የተላበሰ ውሳኔ እንዲሰጡ ሕጎችንና የሙያቸውን ሥነ-ምግባር አክብረው ዲሞክራሲና የፍትሕ ሥርዓቱ እንዲጐለብት የየራሳቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

በአሜሪካ ሀገር የኦሃዩ ስቴት የወንጀል ጠበቆች ማህበር ኘሬዚዳንት ካርሜን ሄርናንዴስ የሚከራከሩበትን ጉዳይ በሚገባ መረዳትን በተመለከተ ሲናገር ትክክለኛና ሚዛናዊ ውሳኔ መስጠት እንዲቻል ዓቃቤ ሕጉም ሆነ ጠበቃው የሚከራከርበትን ጉዳይ አጥንተውና ተዘጋጅተው ችሎት መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚከራከርበትን ጉዳይ ሳያጠናና ሳያዘጋጅ ወደ ችሎት የሚቀርብ ባለሙያ በሽተኛን ሳይመረምር የቀዶ ጥገና ለማድረግ ስራው ወደሚሰራበት ክፍል እንደሚገባ ሃኪም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም መዝገቡን ሳያጤኑ ወደ ችሎት መቅረብና የበሽተኛውን ታሪክና ሁኔታ ሳይመረምሩ የቀዶ ጥገና ማድረግ ውጤቱ አደገኛና ባለጉዳዮችን ወይም ደንበኞችን ለጉዳትና ለሸንፈት የሚዳርግ ነው በማለት ገለፃቸውን አጠናቀዋል፡፡

<u>አቶ አበበ አሳመረ - ጽሑፍ አቅራቢ (ጠበቃና የሕግ አማካሪ)</u>



የጠበቆች የሥነ-ምግባርን ችግር በተመለከተ ለትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ያከናወኑ መሆኑን ጠቁመው በዕለቱ የሚያቀርቡት ጽሑፍም ከዚሁ ጥናት ላይ የተወሰደ መሆኑን እና ለዚህ መድረክ እንዲመጥን ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

አንድ ባለሙያ በሚሰጠው የሙያ አገልግሎት ሊከተለው የሚገባውን ሥነ-ምግባር መርሆዎች ሊፈፅመው የሚገባውን ተገቢ አሠራር በተመለከተ በሕግ መደንገጉ እየተለመደ ስለመሆኑ ጠቅሰው በዚህ ረገድ ሕግና የሕክምና ሙያ ለዘመናት የቆየ የሥነ-ምግባር መርሆዎች ያላቸው መሆኑን ከጠበቃ የሚጠበቁ የሥነ-ምግባር መርሆዎች በቀደመው ጊዜ በልማድ እያደገ የመጣ መሆኑን ለምሳሌ የደንበኛ ሚስጢር መጠበቅ ተጠቃሽ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ ጠበቃው በሕግና በውል የተቀመጡ እንዲሁም ፍትህን በማገዝ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው ስለመሆኑ የሚታመን እንደሆነና ጥብቅና ጥብቅ የሆነ የሥነ-ምግባር ግዴታዎች ካሉባቸው ሙያዎች መካከል ዋኛኛው መሆኑን ጠቁመው ጠበቃው ከፍተኛ የሙያ ሥነምግባር፣ ችሎታና ክህሎት ያስፈልገዋል ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ እነዚህ ግዴታዎች ያሉበት ጠበቃው በአፈፃፀሙ ላይ መነቆዎች መኖራቸው የገለፁት አቶ አበበ የጽሑፋቸው ዓላማም የችግሮቹን በጎርይ፣ የችግሮቹን ምክንያቶች እና የመፍትሔ ሃሳቦችላይ የሚያተኩሩ መሆኑን በመግለጽ የጽሑፋቸውን ወሰን አስቀምጠዋል፡፡

የሙያ ኃላፊነትን በተመለከተ አንድ ሙያ የራሱ የአተገባበር ደረጃ እና ሊወሰድ የሚገባ ጥንቃቄ እንዲሁም ሊያሳይ የሚገበው ባህሪተደንግጎ የሚቀመጥ መሆኑን አስታውቀው እነዚህ መመሪያዎች የሙያ ሥነምግባር ተብለው የሚታወቁ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ የሙያ ኃላፊነትን በመደንገግና ደረጃ በማውጣት ሦስት ሥርዓቶች ወይም አካሄዶች ያሉ ሲሆን እነዚህም፡-

1. Government regulation - የሙያውን የአተገባበረ ደረጃ፣ የጥንቃቄ እርምጃ እንዲሁም የሚጠበቀውን ባሕሪ እና ሥነ-ምግባር መንግሥት በሕግ መልክ ሲያወጣ መሆኑን፤
2. Co-regulation - መንግሥትና የሙያ ማኅበራቱ በጋራ ሆነው ሲያስተዳደሩ ስላለው ሁኔታ፤ እና
3. Self-regulation - የሙያ ማኅበራት በራሳቸው የአባሎቻቸውን የሥነ-ምግባር ደንብ በማውጣት እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች እራሳቸውን ሲያስተዳድሩ ያለውን ሁኔታ መሆኑን በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

በሀገራችን በፌደራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 ላይ ተደንግገው የሚገኙ ሲሆን ይህ ደንብ በውስጡ ጠበቃው ለደንበኛው፣ ለማኅበረሰቡ እንዲሁም ለሌሎች የፍትህ አካላት ያለበትን ግዴታ የሚዘረዝር ሰፊ ሕግ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከሙያው ሥነ-ምግባር ጋር ተያይዞ ዘርፈ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን በሚሰጠው የሙያ አገልግሎት ብቃትና ሥነ-ምግባርን በጥርጣሬ የመመለከት ሁኔታ የተለመደ እንደሆነ በተለያየ አግባብ እንደሚገለፅ ነገር ግን ጉዳዩን መሠረት አድርጎ በጥናት የተደገፈ ቢሆን መልካም እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

ጽሑፍ አቅራቢው ጥናታቸውን ሲያዘጋጁ የተለያዩ መንገዶችን የተጠቀሙ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ከጠበቆች የተሰበሰቡ መጠይቆች፣ በማኅበር የተሞላ መጠይቅ፣ ቀደም ብለው ዳኛ የነበሩ በአሁኑ ጊዜ ጠበቃ በሆኑ ሰዎች የተሞላ መጠይቅ፣ ቁልፍ ተጠያቂዎችን በማነጋገር (Key informant interview) እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን እንደ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የተጠቀሙ መሆኑን አስቀምጠዋል፡፡

የፌደራል ፍ/ቤት ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 በአንቀፅ 2 (3) እና (8) መሠረት ጠበቃ ማለት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ስሙ የተመዘገበ ባለሙያ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን አገልግሎት በክፍያ ወይም ያለክፍያ ሊሆን እንደሚችል ከሕግ ምክር ጀምሮ የተለያዩ ሕጋዊ ሰነዶችን ከማዘጋጀት ሌሎች ሰዎችን በመወከል በፍ/ቤት ቆሞ መከራከርን የሚያጠቃልል እንደሆነ ይህን አገልግሎት ጠበቆች ሲያቀርቡ በሥነ-ምግባር ደንብ ላይ የተቀመጡት ነጥቦች ማክበርና መከተል እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል፡፡ ጠበቆች ፍትህን ለማረጋገጥና የሕግ የበላይነትን ለማስፈን ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ለፍ/ቤት፣ ለባለጉዳይ፣ ለመንግሥትና ለማኅበረሰቡ ከፍተኛ የሆነ ኃላፊነት ያለባቸውና የሚጠበቅባቸውም ግዴታ ሰፊ ነው፡፡

የጠበቆች ሥነ-ምግባር ደንብ ላይ ከተቀመጡት መርሆዎች መካከል ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት፣ ሚስጢር ስለመጠበቅ፣ የጥቅም ግጭት፣ አከራካሪ ጉዳይ ሳይኖር ክስ አለማቅረብ፣ ለተቃራኒ ወገን ቅን መሆን፣ የሦስተኛ ወገን መብቶችን ስለማክበር፣ የአገልግሎት ክፍያ ተመን እና ስምምነት፣ ነፃ የህግ አገልግሎት መስጠት፣ የሙያ ባልደረባን ማክበር፣ አስነዋሪ ከሆኑ ሥነምግባሮች መራቅ፣ ወዘተ የሚሉ ግዴታዎች የሚገኙ መሆኑን የዘረዘሩት ጽሑፍ አቅራቢው እያንዳዳቸው ግዴታዎች ሰፊና ጥልቅ ጽንሰ ሃሳብ የያያዙ መሆናቸ ውን ጠቅሰው እነዚህን ግዴታዎች መተላለፍ በዲሲፕሊን ሊያስጠይቅ የሚችል መሆኑን አስቀምጠዋል፡፡ የመርሆዎቹ ጽንሰሃሳብ ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አከራካሪ ጉዳዮች ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንደሆና ለዚህም የዲሲፕሊን ጉባዔው የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ ወጥ የሆነ አተረጓጎም እንዲኖር ፅሁፎች ቢዘጋጁና ሥልጠና ቢሰጥባቸው መልካም እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በጠበቆች ላይ የሚታዩ የሥነ-ምግባር ችግሮችን በተመለከተ እራሳቸው ጠበቆች፣ የጠበቆች ማኅበርና የቀድሞ ዳኞችና ፍትህ ሚኒስቴር የአሁኑ ጠቅላይ ዐ/ሕግ መረጃ ተጠይቀው የተለያዩ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች ስለመኖራቸው የገለፁት አቶ አበበ እንደሚከተለው ለያይተው ዘርዝረዋል፡፡

**ሀ/ በጠበቆች የተጠቆሙ ችግሮች፡-** ጠበቆች እራሳቸው አለብን የሚሉት ን ወይም በሌላው ጠበቃ ላይ የተመለከቱትን ችግሮች እንዲለዩ መጠየቅ ተሰጥቷቸው በሰጧቸው ምላሾች መሠረት በቀጠሮ ጊዜ መቅረት ወይም ማርፈድ፣ ተዘጋጅቶ አለመቅረብ፣ በዝርዝር አለመመዋዋልና ከደንበኛ ጋር መጋጨት፣ ባለጉዳይን ለማግኘት ፈቃደኛ አለመሆኑን፣ ከተቃራኒ ወገን ጋር መመሳጠር፣ የጉዳይን አዋጭነት አለማየት፣ እውነትን መደበቅ፣ ሌላውን ተከራካሪ መዝለፍ፣ ሌላውን ለማጉላላት የወንጀል ክስ ማቅረብ፣ የደንበኞችን ሰነድ በአግባቡ አለመያዝ፣ በማያውቁት የሕግ ዘርፍ ገብቶ ጉዳይ መያዝ፣ የተሳሳተ ምክር መስጠት፣ ጉቦ ማቀባበል ወዘተ እንደቅደምተከተላቸው ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በችግርነት የተጠቀሱ ናቸው ብለዋል፡፡

**ለ/ በጠበቆች ማኅበራት የተጠቆሙ ችግሮች፡-** የጠበቆች ሥነ-ምግባር ጉዳይ የሚያገባው ሌላኛው አካል የጠበቆች ማኅበራት ሲሆኑ በሌሎች ሀገራት የጠበቆች ማኅበር እጅግ በጣም ጠንካራ እና ጠበቆችም በማኅበሩ አባል የመሆንና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው ያሉት ጽሑፍ አቅራቢው የአባላቶቻቸውን የሥነምግባር ደረጃ ከፍ ከማድረግ በዘለለ የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ የጠበቆችን አቅም በማጎልበት ላይ ጉልህ ሚና ያላቸው ማኅበራት ሲሆኑ በሀገራችን ሁለት ማኅበራት መኖራቸውን ነገር ግን አብዛኛው ጠበቃ የማኅበራቱ አባል አይደሉም ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ለመጠይቁ ምላሽ የሰጠ ሲሆን በጠበቆች ላይ የሚታዩ ችግሮች በሚል የለየውም ዳኞችን በተለያየ መንገድ ለማሳመን የሚደረግ ጥረት፣ ሕጋዊ መሠረት የሌላቸው ክርክሮችን ማቅረብ፣ እራስን ከዳኞች ጋር ባለ ቅውውቅ ውሳኔ ማስገኘት እንደሚችል አድርጎ መቅረብ፣ ለሙያው ክብር አለመስጠት፣ ለሙያው ክብር አለመስጠት፣ በማኅበረሰቡ ዘንድ አልባሌ በሚባሉ ቦታዎች በመገኘት እራስን ለሥነምግባር ጥሰት ማመቻቸት እና ከሌላ ባለሙያ ጋር ያለው ግንኙነት ከቅን ልቦና ውጭ መሆን እንደሆነ ስለመጠቆማቸው በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡

**ሐ/ በቀድሞ ዳኞች የተለዩ ችግሮች፡-** እነዚህ አካላት ቀደም ብለው ዳኞች የነበሩ እና በአሁኑ ጊዜ በጥብቅና ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች ሲሆኑ እነዚህ አካላት በዳኝነት ዘመናቸው የሚያውቋቸውን የጠበቆችን የሥነ-ምግባር ችግሮች የለዩ ሲሆን እነዚህም ለሌላው ተከራካሪ ወገን ተገቢውን ክብር አለመስጠት፣ መዝገባቸውን በሚገባ አጥንተውና ተዘጋጅተው አለመቅረብ፣ ማርፈድ፣

መዝገብ ይዞ አለመቅረብ፣ ደንበኛውን ለማስደሰት ወይም ፍ/ቤትን ለማሳሳት ተገቢነት የሌለው ክርክር ወይም አቤቱታማቅረብ፣ እውነት መደበቅ፣ ከጭብጥ ውጭ የሆነ ክርክር ማቅረብ፣ በቂ ባልሆነ ምክንያት ዳኞችን መክሰስ፣ ፍ/ቤት የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች በተገቢው ጊዜ አለመፈፀምና ለጉዳዩ መበላሸት ምክንያት መሆን፣ ወዘተ የሚሉ ነጥቦችን አንስተዋል ብለዋል፡፡

**መ/ በፍትህ ሚኒስቴር የተለዩ ችግሮች፡-** ይህ አካል የአሁኑ የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ ሲሆን በሥነ-ምግባሩ ደንቡ መሠረት የፌደራል ጠበቆች ተቆጣጣሪ መ/ቤት ነው፡፡ ተቋሙ ለጠበቆች ፈቃድ በመስጠትና በማደስ እንዲሁም የሥነ-ምግባር ጉድለት ክስ ሲቀርብ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን ያለው አካል እንደመሆኑ መጠን ከጠበቆች ሥነ-ምግባር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን በቅርበት የሚያውቅ አካል እንደሆነ ይገመታል ያሉት አቶ አበበ ከተቋሙ ያገኟቸውን መረጃዎች በዝርዝር ያስቀመጡ ሲሆን እንደሚከተለው ተቃኝቷል፡፡

ከ2001 እስከ የካቲት ወር 2003 ድረስ በጠበቆች ላይ 211 የዲሲፕሊን ክሶች የቀረቡ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 67 ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ቀሪዎቹ በተለያየ ምክንያት ማለትም በእርቅ፣ አመልካች ባለመቅረብ፣ ጉዳዩ አያስከስስም በመባሉ፤ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለመኖር፣ በነፃ መሰናበት ወዘተ ክሶቹ ተዘግተዋል፡፡ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጣቸው የዲሲፕሊን ግድፈቶች መካከል የጥብቅና ፈቃድ ሳይኖር በከፍተኛ ፍ/ቤት መከራከር፣ እውነትን አውቆ በተቃራኒው መከራከር፣ ሐሰተኛ ውክልና፣ በአንድ ዓይነት ክስ ለባለጉዳይ ባላጋራ መስራት፣ የደንበኞችን ጥቅም ጠብቆ አለመከራከር፣ ደንበኛን የተጋነነ ክፍያ መጠየቅ፣ ክሱ ያዋጣል በሚል ጀምረው ኂላ አያዋጣም ብሎ መተው፣ የጠበቃን ሥነምግባር ባልጠበቀ ሁኔታ የውርስ አጣሪ ሆኖ መሾም ይገኙበታል ብለውል፡፡ የዲሲፕሊን ክሶቹን አስመልክቶ ሙሉ የሆነ የተደራጀ መረጃ የሌላ ሲሆን ለወደፊት በተደራጀ ሁኔታ ቢቀመጥ በተደጋጋሚ ክስ የሚቀርብባቸውን የሥነ-ምግባር ችግሮች ለመለየትና ሥልጠና ለመስጠጥም አመቺ በመሆኑ ይህ ሊታሰብባት እንደሚገባ አውስተዋል፡፡

በ2001 አሥራ ሁለት ክሶች የቀረቡ ሲሆን አምስቱ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈባቸው ሲሆን የቅጣቶቹ ዓይነትም እገዳ፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እና የገንዘብ መቀጮዎች ናቸው ብለዋል፡፡ በ2002 ደግሞ 162 ክሶች ቀርበው በ56 የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን 23 እገዳ፣ 4 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 28 የገንዘብ መቀጮ፣ 1 ፈቃድን ለዘለቄታው መሠረዝ ይገኙበታል፡፡ በ2005 115 ውሳኔ ያገኙ ክሶች መሆናቸውን፣ በ2006 ዓ.ም. 263 ክሶች ቀርበው 196ቱ ላይ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ በ2007 ከ225 የዲሲፕሊን ክሶች 180 ውሳኔ የተሰጠባቸው መሆኑን፣ በ2008 ወደ 143

የሚሆኑ ክሶች ቀርበው እንደነበረና ፈቃድን ባለማሳደስ ለጊዜው የታገዱ ወደ 59 የሚጠጉ መሆናቸውን በዳታ መልክ ዘርዝረዋል፡፡ በአጠቃላይ ከሚቀርቡ ክሶች በአማካይ ከ8 እስከ 10 በመቶ ጥፋተኛ የሚባል ሲሆን ከተለያዩ የዓለምአቀፍ ደረጃዎች ጋር ሲነፃፀር እጅግ ብዙ መሆኑና እና የሚጠበቀውና ጤናማ ሊባል የሚችለው ግን ከ1 እስከ 2 በመቶ ብቻ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም የዲሲፕሊን ክስም ሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከፍተኛ በመሆኑ ለጥብቅና ሙያ ሕልውና አደጋ ሆኖ ሊወሰድ እንደሚገባ እንዲሁም ማኅበራቱና ተቆጣጣሪው የመንግሥት አካል ልዩ ትኩረት ሰጥቶት ሊሰራበት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ ባለድርሻ አካላት የጠበቆች ሙያና የሥነ-ምግባር ብቃትን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ የሥልጠና መድረኮች ማዘጋጀትና ጠበቃውን መደገፍ፤ ጠበቆች ለህጉ ተገዥ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ፤ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት የዚህ መፍትሔ አካል መሆን እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል፡፡

ፅሁፍ አቅራቢው አቶ አበበ ለጠበቃው ሥነምግባር ችግር ምክንያቶች ምንድናቸው የሚላውን ጥያቄ የዳሰሱ ሲሆን ጠበቃው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ከሚፈጥረው የሥነምግባር ግድፈት ባሻገር ሌሎች ምክንያቶች መኖራቸውን ገልፀው እነዚህ ተጨማሪ ምክንያቶችን መለየት ለችግሩ መፍትሔ ዐይነተኛ ሚና የሚጫወት እንደሆነ ካስታወቁ በኋላ ምክንያቶቹ ወጪያዊ ይሁን እንጂ ከጥብቅና ሥራው ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው አካላት እንደሆኑ እና እነዚህም ፍ/ቤቶች እና ባለጉዳዮች እራሳቸው እንደሆኑ እንደሚከተለው አስቀምጠዋል፡፡

**ሀ/ በፍ/ቤቶች ላይ የሚነሱ ችግሮች፡-** የጠበቃ ሥራ በአብዛኛው ከፍ/ቤት ሥራ ጋር የተገናኘ ሲሆን ግንኙነታቸው መልካም በሆነ ቁጥር የየሥነምግባር ችግሮች የመፈጠራቸው እድል እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን በተቃራኒው በጠበቆችና በፍ/ቤቶች መካከል ያለው ግንኙነት መጥፎ ሲሆን ችግሩ በዚሁ ልክ ከፍ ይላል ያሉት ፅሁፍ አቅራቢው በአንዳንድ ፍ/ቤቶች የሚስተዋሉና ለጠበቃ የሥነምግባር ችግር እንደምክንያት የሚነሱት ነጥቦች መካከል ከጊዜ ወደ ጊዜ የውሳኔ ተገማችነት እየተመናመነ መምጣት፣ አግባብነት የሌለው ተደጋጋሚ ቀጠሮ፣ ክስ በመስማት ወቅት ዳኛ አቋሙን የማሳየት ሁኔታ፣ ለተወሰኑ ጠበቆች የተለየ መስተንግዶ ማድረግ፣ በግልፅ ችሎት ያለማስቻል፣ ጠበቆች በሠዓት እንዲቀጠርላቸው ሲጠይቁ ፈቃደኛ አለመሆን፣ ጭራሽ በሠዓት አንቀጥርም ማለት፣ የጠበቃን አጀንዳ አለመጠበቅ፣ ጠበቃን በባለጉዳይ ፊት መዘለፍና ማንቋሸሽ፣ ተገቢውን ጥሪ ያለማድረግ፣ ለጠበቃ ተገቢውን ክብር አለመስጠት፣ ቀጠሮ ሲደረብና ፈቃድ ሲጠይቅ እምቢተኛ መሆን፣ የጠበቃን ንግግር አለማስጨረስ፣ ለአንድ ተከራካሪ ወገን መቆምና ክርክሩን ማጠናከር፣ ያለበቂ ምክንያት በምስክር ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣ ፍ/ቤቱ በቃል የሚናገረውና በመዝገብ ላይ የሚያሰፍረው የተለያየ

መሆን፣ የአንዳንድ የችሎት ተላላኪዎች ባህሪ አስቸጋሪ መሆን፣ ጠበቃውን ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲገጥመው በቀናነት አለመረዳት ወዘተ ናቸው ብለዋል፡፡ እነዚህ ችግሮች በየእለት ተዕለት የሚያጋጥሙ ችግሮች እንደሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ባለጉዳይ ወይም ደንበኛው ጠበቃውን ሊከስ ይችላል ብለዋል፡፡

**ለ/ ባለጉዳዮች፡-** እነዚህም በጠበቆች ሥነ-ምግባር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው መሆኑ ይታወቃል ያሉት አቶ አበበ ዝርዝር ነጥቦችን ያስቀመጡ ሲሆን ከነዚህ መካከል ባለጉዳዮች ወደ ጠበቃ ሲመጡ ዳኛውን ታውቀዋለህ ብለው የሚጠይቁ መሆኑ፣ ዳኛውን አፈላልገህ ካላገኘኸው በሚል ማስጨነቅና የጠበቃ አበል መክልከል፣ ጠበቃው ሳይመቸው ሲቀር ባለጉዳዩ ለመቅረብ ፈቃደኛ አለመሆን፣ ሚስጢር መደበቅና በተቃራኒ ወገን ጉዳዩ ሲጋለጥ መካድ፣ ከፍተኛ ተጠራጣሪነት፣ ከሌላው ተከራካሪ ወገን ወይም ጠበቃ ጋር ያለውን ግንኙነት በቅን ልቦና አለማየት፣ ብዙ ሰው ማማከርና ከጠበቃው ጋር አለመግባባት፣ ክፍያ ላለመክፈል ማጣጣያ ምክንያት መፈለግ፣ ጠበቃው የሠራውን ሥራ ለሌላ ሰው ማሳየትና እንዲቀነስ ወይም እንዲጨመር መጨቅጨቅ ወዘተ ከደንበኛው የሚነሱ ችግሮች መሆናቸውን አስቀምጠዋል፡፡

በመጨረሻም ለተነሱ ችግሮች የመፍትሔ ሃሳቦች በሚል ያስቀመጧቸው ቁምነገሮች ያሉ ሲሆን ከጠበቃው ከሚነሱ የሥነ-ምግባር ችግሮች ባሻገር ከፍ/ቤቶች፣ ከባለጉዳዮች እና ከሌሎች አካላት የሚመነጩ ለጠበቃው የሥነምግባር ግድፈት ምክንያት የሚሆኑ ነጥቦች መኖራቸው የመፍትሔ ሃሳቡም በዚሁ ልክ ሁሉንም የችግሮች ምንጭ አካታች በሆነ መልኩ መቀመጥ አለበት ያሉት አቶ አበበ የሚከተሉትን የመፍትሔ ሃሳቦች ጠቁመዋል፡፡

1. ጠበቆች የሥነምግባር ደንቡን እንዲጠቁ ማበረታታት፤
2. ስለሥነምግባር ደንቡ ያለውን ግንዛቤ ማዳበር፤
3. የጠበቆች ማኅበራት የራሳቸውን የሥነምግባር ሕግ መቅረፅና ደንቡን የሚተላለፉ ሙያተኞች ላይ ከአባልነት መሰረዝ እስከሚያስችል እርምጃ መውሰድ፤
4. የሥነምግባር ሕጉ ትርጉም ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ዝርዝር የጽንሰሃሳብ ሽፋን የሚዘጋጅበት ሁኔታ ማመቻቸት፤
5. የዲሲፕሊን ክስ ውሳኔዎች ለመረጃ ትንተና እና ለማስተማሪያነት ማዋል፤
6. የዲሲፕሊን ክሶች በቅድሚያ በማኅበራቱ በግልግል ወይም በእርቅ እንዲታዩ የሚደረግበት ሁኔታን መፍጠር፤

7. ፍ/ቤቶችና ጠበቆች ለአንድ ዓላማ የሚሰሩ እንደመሆናቸው መጠን ግንኙነታቸውን የተሻለ እንዲሆን መስራት፤

በአጠቃላይ በመፍትሄዎቹ ላይ በደንብ ከተሰራ መሻሻሎችን ማምጣት የሚቻል መሆኑን ጠቁመው ለዚህ ደግሞ የሙያ ማሕበራቱ ተጠናክረው ንቁ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል ያሉት አቶ አበበ በአሁኑ ጊዜ ማህበራቱ ጠበቆችን ሙሉ ለሙሉ ለማስተዳደር የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሷል የሚል አቋም ባይኖራቸውም ወደዚህ መምጣት የሚስፈልግ ስለመሆኑ አስረድተው አጠናቀዋል፡፡

## ወ/ሮ ትደነቂያለሽ ተስፋ - ጠበቃና የሕግ አማካሪ

1. በጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባዔ የሚታዩ እና ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ብዛት ያላቸውና ጊዜም የሚፈጁ መሆናቸው በመድረኩ ከቀረቡ ስታስቲክሶች መረዳት እንደሚቻል ጠቁመው ጉዳዩ የሚመራበት ሥነሥርዓትን አስመልክቶ የዲሲፕሊን ክሱ እንደመጣ ነው ጠበቃው መልስ እንዲሰጥበት ጥሪ የሚደረግለት ወይንስ ጠበቃው ከመጠራቱ በፊት ጉዳዩ ለዲሲፕሊን ብቁ ስለመሆኑ የያስቀርባል አያስቀርብም የሚለው ይታያል?
2. የጠበቆች የ50 ሠዓት አስገዳጅ የነፃ የሕግ ድጋፍ መስጠት ኃላፊነትን በተመለከተ በሙያ ማኅበራቱ በሚቀርብ ጥያቄ የሚሰጡ አገልግሎቶች ለምሳሌ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበርና በሌሎችም ጠያቂነት የሚሰጡ አገልግሎቶች በዚህ የ50 ሠዓት ግዴታ ውስጥ የመሸፈናቸው ሁኔታ ወጥነት ይጎድለዋል፡፡ በዚህ በኩል ያለው ወጣገብነት ምንድነው?
3. ከጠ/ዐ/ሕግ ለነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ለጠበቆች የሚላኩ አቅም የሌላቸው ባለጉዳዮችን በተመለከተ የጉዳዩ አዋጭነት እንዲሁም ጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚችለው በጥብቅና አገልግሎት መሆን አለመሆኑ ላይ በቅድሚያ የማየት ሁኔታ አለ ወይ?

የሚሉ ሦስት ጥያቄዎችን አንስተዋል፡፡

## አቶ አለማየሁ ፅጌ - የኢ/ሕ/ባ/ማሕበር አባል

የሕግ ባለሙያ እንጂ ጠበቃ አለመሆናቸውን ጠቅሰው የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንስተዋል፡፡

1. የጥብቅና ፈቃድ ለመስጠት 5 ዓመት እና በሕግ ዲግሪ ስለመኖሩ የትምህርት ማስረጃ ይፈልጋል፡፡ እኔ ለምሳሌ ፈሪላንሰር በመሆን ረዘም ያለ ጊዜ የሰራሁ ሲሆን ደመወዝተኛ በመሆን ፔይሮል ላይ በመግባት ስሰራ የቆየሁ ባለመሆኔ ምክንያት ፈቃዱን ለማግኘት ተቸግሬአለሁ፡፡ የኢ/ሕ/ባ/ማህበር በሚሰጠው ተከታታይ ትምህርት ላይ ስለመካፈሌ ማስረጃ

ተሰጥቶኝ አስጠርገዬ ይዤዋለሁ ነገር ግን ፈቃዱን ማግኘት አልቻልኩም፡፡ የመግቢያው ፈተና በቂ አይደለም ወይ? ፈታነው እጅግ በጣም ጥሩ እና አቅም ያለውን መለየት የሚችል በመሆኑ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡

2. ሀገራችን እያደገች ነው ያለችው ከውጭ የሚመጡ ሰዎችም በደፈናው የህግ ባለሙያ አይሉም ይልቁኑ በታክስ፣ በኢንቨስትመንት፣ በኮሜርሻል ሕግ፣ በኢንሹራንስ፣ በአእምሯዊ ንብረት መብት ወዘተ ስፔሻላይዝ ያደረጉ ባለሙያዎች በሚል ነው የሚጠይቁት በመሆኑም በሀገራችንም ይህ ዓይነት ትሬንድ እንዲለመድና ጠ/ዐ/ሕግም ይህን ጉዳይ አይቶ ለይቶ ቢሰራ መልካም ነው ብለዋል፡፡
3. በመጨረሻም በጥናት ላይ የተረኮዘ ከጥብቅና ወደ ዳኝነት የሚኬድበት ሥርዓት ቢፈጠር መልካም እንደሆነ ጠቁመው ይህ ዓይነት አሠራር በሌሎች ሀገራት ተግባራዊ እንደሆነ ገልፀው የጥብቅና ሙያ የእድሜ ገደብ ተደርጎለት ወደ ዳኝነት የሚኬድበት ሁኔታ ቢኖር ለፍትህ ሥርዓቱ በተለይም ለዳኝነት ሥርዓት መልካም እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡

<u>አቶ በሻዳ ገመቹ - አወያይ</u>

አቶ አለማየሁ ያነሱት ነጥቦች መሠረታዊ ናቸው ነገር ግን ከጭብጣችን እንዳንወጣ የሚል ማሳሰቢያ ሰጥተው ጥያቄ፣ ሃሳብ አስተያየት እንዲቀጥል መድረኩን ለታዳሚው በድጋሚ መልሰዋል፡፡

<u>አቶ ገ/እግዚአብሔር ገብረጊዮርጊስ - የኢ.ሕ.ባ.ማኀበር ም/ፕሬዝዳንት</u>

1. በቀረበው ፅሁፍ መሠረት በጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባዔ ከታዩ ጉዳዮች ፈቃድ አለማደስ ስለመሆኑ በአሃዝ የተገለፀ ሲሆን በመቶኛ ስሌቱም ወደ 35 በመቶ ከመሆኑም በላይ ከሌሎች ጠዲሲፕሊን ጉዳዮች የላቀ ቁጥር እንዳለው የተመለከትን መሆኑን ገልፀው የጥብቅና ፈቃድ የማደስ እና በወቅቱ ያለማደስ ጉዳይ በምን አግባብ የሥነ-ምግባር ጉዳይ ሆኖ ለዲሲፕሊን ይቀርባል በማለት የጠየቁ ሲሆን ፈቃድን ማደስ በሌሎች የንግድ ዘርፎች ጭምር የሚጠበቅ ጉዳይ ሆኖ አለማደስ ግን አስተዳደራዊ ቅጣትን ሊያስከትል ከሚችል በዘለለ ወደ ዲሲፕሊን የሚሄድ ከሆነ፣ ይህ ደግሞ የጠበቃው ማኅደር ውስጥ ፋይል የሚደረግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ችግር ሊያመጣ አይችልም ወይ?
2. የጥብቅና ፈቃድ ሲታደስ አንድ ወር ቀደም እንዲል ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ የ1 ወር ቀደም ማለት ጥርቅም በ12 ዓመት ውስጥ ግብር የተከፈለበትን አንድ ዓመት ይዞ የሚሄድ በመሆኑ ይህ እንዴት ይታያል?

3. የጠበቆች የቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ 3 መንገዶች እንዳሉ ከመድረክ የተገለፀ መሆኑን እነዚህም government regulation, co-regulation እና self-regulation መሆናቸውን አስታውሰው self-regulation በሚመለከት በበለፀጉ ሀገራት ይህ ተሞክሮ ያለና በማህበራት በኩል የሚስተናገድ ሲሆን ሙሉ በሙሉ ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ ናቸው ለማለት ግን የሚያስደፍር አይመስለኝም ምክንያቱም የሚቋቋሙበት የመንግሥት statuteን ጨምሮ አንድ አንድ ጥሰቶችን በሚመለከት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን supervision እና sanction ሊኖር የሚገባ ይመስለኛል በማለት ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

------------------ ---- -----------------

1. የጥብቅና ፈቃድን የሚሰጠው የወንጀል ተከራካሪያችን የሆነው የቀድሞው ፍትህ ሚኒስቴር የአሁኑ የፌ/ጠቅላይ ዐ/ሕግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ጠበቆች ሲያጠፉ በዲሲፕሊን ቀርበው ጉዳያቸው ይታያል ነገር ግን ዐ/ሕግ ሲያጠፋ ተቀጥቶ ያውቃል ወይ?
2. አንድ ተጠርጣሪ በወንጀል ምርመራና ክስ ጉዳይ ብዙ ዓመታትን ሊታሰርና ኋላም ነፃ ሊባል ይችላል፡፡ ለዚህ ያለአግባብ ለተጎዳበት ማንን ይጠይቃል? ሲሉ ጥያቄያቸውን አክለዋል፡፡

<u>አቶ ዜና ደባሱ - የኢ/ሕ/ባ/ማኅበር አባል</u>

ጠ/ዐ/ሕግ ተከታታይ የህግ ትምህርትን ማዘጋጀት የሚቸግረው ምንድነው? ከዳኞች፣ ከዐቃቢያነ ሕግ እንዲሁም ከተለያዩ ማኅበራትን አሳታፊ የሚያደርግ ሥልጠናን ማዘጋጀት አሠልጣኝም ማግኘት እንዴት አስቸጋሪ ሊሆን እንደቻለ እንዲብራራላቸው ጠይቃዋል፡፡

<u>አቶ ታደለ ጉታ - ጠበቃና የሕግ አማካሪ</u>

እዚህ ያለን ሰዎች ጠበቆች ነን፣ ጠ/ዐ/ሕግ እራሱ ጠበቃ ነው፡፡ የጥብቅና አገልግሎት objectivity; transparency; accountability ወዘተ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሁላችንም to the best interest of our client መስራት መቻል አለብን፡፡ ሁላችንም የመንዋኘው አንድ የሙያ ገንዳ ነው ስለዚህ ተፃራሪ እና ተወዳዳሪ አይደለንም፡፡ የጥብቅና ዘርፍ እንደ አንድ አገልጋይ institution እውቅናና ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሠጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀፅ 24 (8) መሠረት የዲሲፕሊን ጉባዔው አንድ ክስ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ ማቅረብ እንዳለበት በቂ ምክንያት ሲያጋጥም ለ3 ወር ሊራዘም ይችላል የሚል ሲሆን ይሁን እንጂ አሁን በየቦታው kangaroo court ተቋቁሟል በstatutory period

of limitation የማይገዛ፤ ስለሆነም ይህ ለምን challenge አይደረግም፤ ለምን የራሱን ጥፋቶች አያርምም፣ ጥብቅና የሰው ሕይወትና ንብረት በውስጡ የያዘ ነው መከበር መቻል አለበት፤ ሁለቱም እኩል መጠየቅ አለባቸው፡፡

<u>አቶ መስፍን አዲሴ - የሕግ ጠበቃና አማካሪ</u>

1. ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማኅበራት ጠበቆች የጥብቅና አገልግሎቶች ይሰጡ የነበረ ሲሆን በአዋጁ ምክንያት የመክፈል አቅማቸው በመቀነሱ ብዙ ጠበቆችን የቀነሱ መሆኑ የሚታወቅ ይሁን እንጂ አንድ አንድ ጠበቆች ለነዚህ ተቋማት በነፃ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ መሆኑ ይታወቃል በመሆኑም ይሄ ዓይነት አገልግሎት በ50 ሰዓት ግዴታ ውስጥ ሊካተት የሚገባ መሆኑን ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡
2. ነፃ የህግ ድጋፍ እንዲሰጣቸው በጠ/ዐ/ሕግ የሚላኩ ሰዎች ወደ ጠበቃው ከመላካቸው በፊት ጉዳያቸውን አስረድተው ለጉዳዩ መፍትሔ የሚሰጠው በጥብቅና አገልግሎት ስለመሆኑ በተቋሙ ታምኖበት ቢሆን ጥሩ እንደሆነ ጠቁመው የተላከለት ጠበቃ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ አዋጭ እንዳልሆ የምክር አገልግሎት ሲሰጣቸው በዲሲፕሊን እንደሚከሱ የሚዝቱ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ቤቱን በሕጋዊ መንገድ ሸጦ ክፍያ የተቀበለ ሰው ክፍያውን አልሰጡኝም በሚል ተልኮ ሁሉም ማስረጃዎች ገንዘቡን በአግባቡ ስለመቀበሉ የሚያስረዱ ሆነው ሳለ ካልተከሰሰልኝ ሲሉ የነበሩ አልፎም ውሻቸው በተሸጠው ቤት በር ፊት እየቆመ በመሆኑ ፎቶ ተነስቶ ገንዘብ ላለመቀበሌ ማስረጃ ይሆናል የሚሉም እንዳሉ በምሳሌነት አስቀምጠዋል፡፡
3. ለነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በጠ/ዐ/ሕግ በኩል ለጠበቆች ሲላኩ financially overburden ያደርጓቸዋል፡፡ ጠበቆች ቀለብ እስከመቁረጥ ድረስ የሚደርሱበት አግባብ ነው ያለው፡፡ ማስማት የተሳነው ባለጉዳይ እንደሆነ ለምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ክፍያን ይጠይቃል፤ የምሳ፣ የትራንስፖርት ወዘተ ወጪዎች ይከፈላሉ በመሆኑም እነዚህ ተገልጋዮች ወደ ጠበቃው ሲላኩ የሚያገኙት አገልግሎት ሙያዊ ብቻ ስለመሆኑ ቢነገራቸው መልካም እንደሆነ አሳስበዋል፡፡
4. ሀምሌ እና ነሃሴ የጥብቅና ፈቃዳቸውን የሚያሳድሱ ሰዎችን በሚመለከት የግብር መክፈያ ጊዜ በመሆኑ እና የችሎት መደራረብ ሁኔታ በመኖሩ ምክንያት ሊዘገዩ የሚችሉ መሆኑን በመገንዘብ ተገቢው የመጠበቅ ሁኔታ ቢኖር መልካም እንደሆነ አውስተዋል፡፡

## <u>አቶ አበራ አቻ - ጠበቃና የሕግ አማካሪ</u>

1. በጠበቆች ላይ የተነሱ ችግሮችን ተቀብለን ማረም ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው በሌሎች አካላት ደግሞ የሚፈፀሙ ማለትም በፖሊስ፣ በዐ/ሕግ እንዲሁም በፍ/ቤት ያሉትን ችግሮች ከሌላም አካል ተጋብዘው ተሳታፊ የሚሆኑበት አግባብ ቢኖር ጥሩ እንደሚሆንና ለውጥ ማምጣት የሚቻል ስለመሆኑ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡
2. በጠ/ዐ/ሕግ በኩል ለነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ደንበኞችን ሲልኩ የክርክሩ ፍሬ ነገር መርምረው፣ አዋጭነቱን ገምግመው ሊልኩ እንደሚገባ፤ ድሃ ተብለው የሚመጡ ሰዎች በትክክልም ድሃ ስለመሆናቸው አነስተኛ ምርመራ እነኳ ቢደረግ የተሸለ እንደሚሆን ገልፀው፤ እነዚህ ሰዎች የምክር አገልግሎት ተሰጥቷቸው አዋጭ እንዳልሆነ ሲነገራቸው ጠበቃው እምቢ ብሎኛል በማለት የመክሰስ ሁኔታ በስፋት ያለ በመኖሩ ይህ በጠበቃው ላይ የችግር ምንጭ እየሆነ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
3. ፈቃድ በወቅቱ ያለማሳደስ ጉዳይ የዲሲፕሊን ጉዳይ ሆኖ ማቅረቡ ላይ እንደማይስማሙ ገልፀው አንድ አንድ ባለሙያዎች ሥራውን ሳይሰሩ የሚቆዩ ያሉ መኖራቸውንም ግምት ውስጥ ማስገባት ብሎም በአስተዳደራዊ መንገድ እልባት ሊያገኝ የሚችል ስለመሆኑ የበኩላቸውን ገልፀዋል፡፡



## አቶ ፈቃዱ ደምሴ - ጽሑፍ አቅራቢ

በተሳታፊው በግልፅ የተነሱ ሃሳብ አስተያየት እንዲሁም ጥያቄዎች ለወደፊት በጋራ ለምንሰራቸው ሥረዎች መልካም አገጣሚ እንደሚሆን ገልፀው በጠበቆች ላይ የሚነሱ የሥነምግባር ችግሮችና ለዲሲፕሊን የሚቀርቡ ጉዳዮች በሚል ወደ ራሳችን ወደ ውስጥ መመለከት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ጠ/ዐ/ሕግ ጠበቆችን ለመቅጣት ወይም ለመክሰስ ነው ሁልጊዜም የሚፈልገው የሚሉ አንድ አንድ ጠበቆች እንዳሉ ጠቅሰው የዲሲፕሊን ክስ በሚመለከተው ሰው በቃል ወይም በፅሁፍ የሚቀርብ ሲሆን የቀረበው አቤቱታ ወይም ክስ በደንቡ መሠረት ሊያስጠይቅ የሚችል መሆኑ አለመሆኑ ላይ ምርመራ ተደርጎ የሚጣራ ሲሆን ወደ ዲሲፕሊን ጉባዔ ከመላኩ አስቀድሞ የሚታይና እልባት የሚያገኝ መሆኑን በዚህም ምክንያት ብዙ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ጠበቃ መልስ እንዲሰጥበት ሳያስፈልግ አያስቀርብም ተብለው የሚቀሩ ብዙ ጉዳዮች ያሉ መሆኑን አበክረው ገልፀዋል፡፡ የወንጀል ክስ የሚሆን እንደሆነም ለኮሚቴው የማይላክ መሆኑን አቶ ፈቃዱ አክለው ተጨባጭ ምሳሌዎችንም አንስተዋል፡፡

ጉዳዩ ለዲሲፕሊን መቅረብ ያበት ስለመሆኑ ከታመነ ለዲሲፕሊን ጉባዔ ተልኮ በፓናል ከታየ በኋላ ሚያስቀርብ እንደሆነ ጠበቃው መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉባዔው ለሚኒስትሩ/ ለጠ/ዐ/ሕጉ የውሳኔ ሃሳብ የሚቀርብ ሲሆን ሚኒስትሩ ካመኑበት የሚፀድቅ ወይም የሚሻር ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላም ይግባኝ መብት ሆኖ ለከፍተኛ ፍ/ቤት የሚቀርብበት የሕግ ሥርዓት መኖሩን አብራርተዋል፡፡

የዲሲፕሊን ውሳኔ ላይ የጥራት ችግር አለ የሚባል እንደሆነ ችግሩ የአንድ አካል ብቻ እንደሆነ ሊወሰድ የማይገባ መሆኑን ጠቅሰው ጉባዔው የሚዋቀረው ከጠበቆች ማኅበር፣ ከፍ/ቤት እና ከጠ/ዐ/ሕግ መሆኑን የጠቀሱት ፅሁፍ አቅራቢው ከሶስቱም አካላት የሚውጣጡ ሰዎች ካላቸው የሥራ ባህርይ እና ጫና ጋር ተያይዞ የውሳኔ ጥራት ችግር ሊያገጥም ይችላል ብለዋል፡፡

ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ለመስጠት በዋናነት ከቀበሌ የሚመጣን የድህነት ማስረጃ እንደመስፈርት የሚጠቀሙ መሆኑን ነገር ግን ድህነት በራሱ መልክ ያለውና አገልግሎት ፈላጊውን በማየት ብቻ ድህነትን መገመት የምንችል መሆኑን ገልፀው ጠበቃው ሙያዊ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚላኩ ይሁን እንጂ የተለያዩ ጠበቆች በመልካም ፈቃዳቸው የምሳ፣ የትራንስፖርትና መሠል ወጪዎችን እንደሚሸፍኑ መረጃዎች አሉን ተለቅ ያለ ገንዘብም በመርዳት መንፈስ የሚሰጡ ጠበቆችን አመስግነው ሕግን ከውስጣችን በፍላጎታችን የምናደርገው እንጂ ግዴታ አለመሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ አንድ አንድ ተገልጋይ ደግሞ ክፍያን የሚጠብቅም ሊገጥም የሚችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አቶ ፈቃዱ የጥብቅና ማሳደስ የዲሲፕሊን ጉዳይ ስለመሆኑ ሲያብራሩ አንድ ጠበቃ የፈቃዱ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት 1 ወር አስቀድሞ ሊያሳድስ እንደሚገባ ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ፈቃዱን የማደስ የሥራ ኃላፊነት ያለብን ሰዎች ደግሞ ስልክ በመደወል በተደጋጋሚ በማስታወስ ነው ፈቃድ እንዲያድሱ የምናደርገው አንድ ሰው ፈቃዱ ሳይታደስ በፍ/ቤት የሚቆም እንደሆነ ይህ አግባብነት የለውም ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ከግብር ጋር በተያያዘ የጥብቅና ፈቃድ ማሳደሻ ጊዜ ይራዘምልኝ በሚል የሚጠይቅን ሰው በአግባቡ የሚስተናገድ መሆኑ ልብ ሊባል እንደሚገባ አሳውቀው የጥብቅና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ጠበቆችን ለመደገፍ የተቻለውንና የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፡፡ ሥልጠናን በተመለከተ ሁለት መርሃግብሮች ተዘጋጅተው የነበሩ ቢሆንም ከፌ/ጠ/ዐ/ሕግ መቋቋምና መዋቅር ጋር በተያያዘ ሥልጠናዎች በታቀደላቸው መሠረት ሊከናወኑ አለመቻላቸውን ገልፀዋል፡፡

## <u>አቶ አበበ አሳመረ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

Self-regulationን በተመለከተ አሁን ባለንበት ደረጃ የሚቻል እንደማይመስላቸው ነገር ግን ሌሎች ባለሙያዎች ይቻላል ብለው የሚያስቡ መኖራቸውን ጠቁመው፡፡ self-regulation professional community vibrant እና activist መሆንን ይጠይቃል ያሉት አቶ አበበ የተለያዩ ማኅበራት ወደ መምጣትን ይጠይቃል ብለዋል፡፡ በራስ መተዳደር ማለት ግን ከምንግሥት ነፃ መሆን ማለት ግን እንዳልሆነ ገልፀው መንግሥት stake እንዳለው አስታውቋል፡፡ ለምሳሌ የኦዲት ቦርድ የተቋቋመበት አግባብና መንገድ እጅግ ጥሩ የሆነ ተሞክሮ ሊሆን እንደሚገባም አክለዋል፡፡ ሌላው ለself-regulation መንግሥትም ready የሆነ አይመስለኝም ብለዋል፡፡ self-regulation NGO ስለሚሆን የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆን የሚገባው ማሃል ላይ ያለውን አማራጭ ማስቀደም ተገቢ እንደሚሆን አስቀምጠዋል፡፡

## <u>አቶ በሻዳ ገመቹ - አወያይ</u>

እራስን ማስተዳደር ላይ መስራት እንደሚቻል የገለፁት አወያዩ አንድ የማኅበር ጥላ ስር ሁነን እርስ በእርስ የምንተዋወቅ በመሆኑ፣ ጠንካራ የሆነ ማኅበርን መመስረት ይገባናል ብለዋል፡፡ ማህበራት ሁለት ብቻ አለመሆናቸውን ገልፀው በክልሎች ማኅበራት መኖራቸውን አስታውሰው እነዚህ አካላት ለዚህ ጉዳይ ቁርጠኛ ከሆኑ መስራት የሚቻል መሆኑን የባለጉዳዮችን ጉዳይ በአግባቡ እያስተዳደርን የራሳችንን ጉዳይ ማስተዳደር እንዴት አይቻለንም? በማለት የጠየቁ ሲሆን ጠበቆች የንግድ ፈቃድ ያውጡ ሲባል ጠበቆች ነጋዴ አይደሉም በማለት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲቆም ያደረጉት በአማራ ክልል የሚገኙ ጠበቆች የሚመለከተው አስተዳደር በማነጋገር እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ የባለሙያው ማኅበር ሁለት ብቻ አይደለም ብዙ ነው የክልሎችን ጨምሮ በማለት አንድ ላይ ሆነን ትንሽ ትንሽ ገንዘብ

ብናዋጣና ንቁ በመሆን የምንሰራ ከሆነ እራሳችንን ማስተዳደር የምንችል ስለመሆኑ ነው የሚሰማኝ በማለት ከአቶ አበበ ጋር ያላቸውን የአቋም ልዩነት አስቀምጧል፡፡

## አቶ ወንድሙ ኢብሣ - ጠበቃ እና የሕግ አማካሪ

ሁለቱንም ፅሁፍ አቅራቢዎች አመስግነው ትምህርቱም ወቅታዊ ስለመሆኑ ገልፀዋል፡፡ ሀገሮች፣ ማህበራት እንዲሁም ሕዝቦች በሕግ የሚተዳደሩ ስለመሆኑ ጠበቆች ደግሞ ብዙ የሕይወት ተሞክሮ ስላላቸው የላቀ ደረጃ ይሰጣቸዋል ምክንያቱም ሁላችንም የምንሰራው የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ መሆኑን የብዙ ሀገር መሪዎችም የሕግ ባለሙያዎች ናቸው ያሉት አቶ ወንድሙ ሙያችን በላቀ ሁኔታ ከፍ ለማድረግ የሕግ ልዕልናን ማረጋገጥ አለብን ብለዋል፡፡

የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉዳይ ውጫዊ ምክንያት የዳኞች ሥነምግባር ጭምር አስቸጋሪ በመሆኑ ነው ያሉት ሃሳብ ሰጭው ድሮ ዳኞች ገበሬን የሚያከብሩ አሁን ያሉት ደግሞ የሚሳደቡ ናቸው ብለው አክለዋል፡፡ ይህ ማለት ግን ጠበቆች ጋር ችግር የለም ማለት አይደለም በተለይ የገንዘብ ጥቅምን መሠረት የሚያደርጉ ባለሙያዎች መኖራቸው የማይካድ ነው ብለዋል፡፡ ለምክር እናስከፍላለን ብሎ በየቢሮ መለጠፍ የሙያውን ክብር ይቀንሳል ያሉት አቶ ወንድሙ ይህ ዓይነት የምክክር መድረክ ቢቀጥል፤ ማቴሪያሎች ቀደም ብለው ቢሰራጩ በተለይም የሥነ-ምግባር ደንቦች መልካም እንደሚሆን በመግለፅ አጠናቀዋል፡፡

## አቶ ታምራት ኪዳነማርያም - የማኅበሩ የቀድሞ ፕሬዝዳንት

ጽሑፍ አቅራቢዎችንና አወያዩን አመስግነው የቀረበው ጽሑፍ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነ ገልፀው በወጭ ሀገራት ወደ 40 በመቶ የሚጠጉ የተከታታይ ትምህርቶች በጠበቆች ሥነምግባር ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ መረጃ በመስጠት እራስን በራስ ከማስተዳደርን በተመለከተ የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያዎች ማህበርና ሌሎች ማህበራት አንድ መሆን እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡ የዩጋንዳ ተሞክሮን የጠቀሱት የቀድሞ የማህበሩ ፕሬዝዳንት አንድ ለመሆን ፕሮፌሽናል የሆነ ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልገው ካሳሰቡ በኋላ ማኅበሩ እራሱ የራሱን የስነምግብር ደንብ ማውጣት እንደሚገባውና መንግሥትም ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ማኅበራችን ሌሎች ማዕከላት እንዳሉት ሆኖ በልደታ ነፃ የህግ ድጋፍ መስጫ ማዕከል ያለ ሲሆን ማዕከሉ የምክር እና የጽሑፍ አገልግሎት ብቻ በመስጠት ላይ የተሰማራ ሲሆን ጠበቃ መቅጠር ለማይችለው የህብረተሰብ ክፍል ጠበቆች ቢቆሙላቸው እና ከ50 ሠዓቱ የነፃ የሕግ ድጋፍ ጋር

የሚቀናጅበት ሁኔታ በጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር በኩል እንዴት ነው የሚታየው ሲሉ የጠየቁት አቶ ታምራት በሌላ አስተያየታቸው በያዘው ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት የለኝም በሚል ወደ ሌላ ጠበቃ ያስተላለፈው ጠበቃ በዲሲፕሊን መጠየቁ አግባብ እንደማይመስላቸው ይልቁኑ ሊመሰገን ይገባ እንደነበር ገልፀው የጥብቅና ሥራ ለዕድቅ (philantrophy) የሚሰራ ባይሆንም ለትርፍ የሚሰራ የንግድ ሥራ አይደለም ብለዋል፡፡ ለጥብቅና ሥራ ማስታወቂያ ያስፈልጋል ብለው አክለዋል፡፡



<u>ወ/ሮ ወይንሸት ከበደ - ጠበቃ/ የማኅበሩ አባል</u>

1) 50 ሠዓት የሚለው ግልፅ እንዳልሆነ ጠቅሰው አንድ ጉዳይ 3 እና 4 ዓመት ይፈጃል ስለዚህ 50 ሠዓት ሲሞላው ጠበቃ ጉዳዩን መከታተል ያቆማል? ሲሉ ጠይቀዋል፡፡
2) የሥነ-ሥርዓት ሕጉ አንቀፅ 42 (1) (ሀ) በሥራ ላይ አይውልም፡፡ ፍ/ቤቱ ይዝጋው ይላሉ ዐ/ሕጎች በመሆኑም መነጋገር ከባድ ሆኖዋል ብለዋል፡፡
3) ጠበቆች ከመንግሥት መ/ቤት ውስጥ ጥሩ አርዓያ የነበራቸውና ጠንካራ ሠራተኞች የነበሩ ነገር ግን ወደ ጥብቅና ሙያ መጥተው ካባ ሲቀይሩ ስማቸው እንዲጎድፍ ያደርጋሉ፡፡ ጠበቃውን ዝቅ የማድረግ ሁኔታ አለ፡፡ አብዛኛው ጠበቃ መልካም ሥነምግባር ያለው ነው፡፡ ዳኞች አካባቢ ከአለባበሳቸው ይጀምራል ብለዋል፡፡
4) ጠበቃ ስፔሻላይዝ እንዲያደርግ እንዲሁም ፈቃዱም በዚሁ መልክ ቢሰጥ ጥሩ እንደሆነ ገልፀው ዳኞችም በዚሁ ልክ ስፔሻላይዝ ቢያደርጉ ጥሩ ነው ብለዋል፡፡

5) የሕግ ምክር እናስከፍላለን መባሉ ተገቢ ነው፡፡ በባለጉዳዮች በኩል በአብዛኛው ያለው ችግር ጉዳያቸው ሲያልቅ ቀሪ ክፍያን አይፈፅሙም ብለዋል፡፡

<u>አቶ ተሾመ ነዳ - ጠበቃ</u>

የዲሲፒሊን ጉባዔ መኖር አስፈላጊነት ላይ ጥያቄያቸውን ያቀረቡ ሲሆን ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ ይዘን የምንሄደው ወደ ሚኒስትሩ ነው ሚኒስትሩ ደግሞ ለአማካሪዎች ይመራሉ አማካሪዎቹ ደግሞ የሚወስኑት የዓይን ቀለም አይተው ነው የሚወስኑት ሚኒስትሩ አያዩትም ብለዋል፡፡ ጉባዔው የወንጀል ጉዳዮችን እንኳ ያያል ይሄ ተገቢ አይደለም ሲሉ ተደምጠዋል፡፡



<u>አቶ ፍቃዱ ደምሴ - ጽሑፍ አቅራቢ</u>

እራስን በማስተዳደር ረገድ የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደር በመሻሻል ላይ ያለ ሲሆን የ50 ሠዓት ጉዳይም ከዚሁ ጋር ተያይዞ ተነስቶ ሕጉ ሲሻሻል ቢነሳ መልካም እንደሆነ ጠቁመው በዚህ አግባብ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችል ነው ብለዋል፡፡ ጠቅላይ ዐ/ሕግ ኬዝ ነው የሚሰጠው 50 ሠዓት የሚለው በአፈፃፀም ረገድ አስቸጋሪ ሲሆን አንድ አንድ ጉዳዮች በቀላሉ እልባት የሚያገኙ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ውስብስብ ናቸው፡፡ ጉባዔውን በተመለከተ ሁሉም መ/ቤቶች የሠራተኞችን የዲሲፒሊን ጉዳይ የሚያዩ አካላት መኖራቸውን ጠቁመው ጉባዔው አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ ፈቃድ ያላሳደሰ ይቀጣል ነገር ግን ቀደም ብሎ ያሳወቀ ሊራዘምለት ይችላል ብለዋል፡፡

**አቶ በሻዳ ገመቹ - አወያይ**

ጠበቃ ውል ሲዋዋል ቅድመ ክፍያ ተቀብሎ ጉዳዩ ካለቀ በኋላ ቀሪ ክፍያ መቀበል ላይ ችግር አለ ያሉት አወያዩኦሮሚያ ክልል ራፖር ጠሃፊም ፈቃድ አውጥቶ ነው የሚሰራው፤ ለወንጀል የአገልግሎት ዋጋ ተመን ወጥቶለት ነው፡፡ የጥብቅና ገቢ ግብርም ተለይቶ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሙያ ትልቅና ቫይብራንት መሆን መቻል አለበት ይህን ማድረግ ለጠበቃው ቀላል ነው ብለዋል፡፡

**አቶ አበበ አሳመረ - ጽሑፍ አቅራቢ**

ጥብቅና ንግድ ነው አይደለም የሚለው አልተቆረጠም ፡፡ የግብር አከፋፈል ልዩነት አለው፡፡ የኦሮሚያ ጥሩና ቁርጥ ያለ ክፍያ ነው፡፡ በፌደራልም ሆነ በክልሎች የግብር ጉዳይ አስቸጋሪ ሆኖዋል ያሉት ንግድ ነው የሚባል ከሆነ ምናስመዘግበው የቤታችንን የቤት ቁጥር ሳይሆን የተከራየነውን ነው ሌሎች ብዙ ውስብስብ ነገሮች ይኖሩታል ብለዋል፡፡ የመኪኖቻችንም ኮድ ይየራል ከተቀናሽና ከተመሳሸ ጋርየተያያዙ ነገሮች ይኖራሉ በመሆኑም uniformity ensure ለማድረግ አንድ መድረክ ሊያስፈልግ እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

**አቶ ቴዎድሮስ ምህረት - የኢ/ሕ/ባ/ማኅበር ፕሬዝዳንት**



ብዙ አካላትን በውይይት መድረኩ ላይ እንዲገኙ ጋብዘን ያሉ ሲሆን ከጠቅላይ ዐ/ሕግ የጥብቅና አስተዳደር አቶ ፈቃዱን፣ የሕግ አማካሪና ጠበቃ የሆኑት አቶ አበበን ላቀረቡት ጽሑፍ እንዲሁም አቶ በሻዳ ገመቹ አመስግነው የጠበቆች የሙያ ሥነ-ምግባርን በማኅበሩ በኩል እየተዘጋጀና የዜሮ ድራፍት ደረጃ ላይ እንደሆነ ጠቁመው እራሳችንን ማስተዳደር እንችላለን የሚል እምነት እንዳላቸው ጠቅሰው

ሌሎች ተመሳሳይ መድረኮች እንደሚኖሩና ተሳታፊዎችንም እንደሚጋብዙ ገልፀው የመድረኩ ተሳታፊዎች በሙሉ ጥሪውን አክብረው ስለተገኙ በማኅበሩ እና በራሳቸው ስም ምስጋና አቅርበው ውይይቱ ከቀኑ 7፡30 ላይ ተጠናቋል።